**CONSULATE GENERAL OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC ETHIOPIA IN LOS ANGELES**
በሎስ አንጀለስ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ቆንሱላ ጀኔራል
3250 WILSHIRE BLVD, SUITE #1101 LOS ANGELES, CA 90010

ከታህሳስ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በአዲሱ የኢሚግሬሽን የአገልግሎት ክፍያ ተመን መመሪያ መሰረት የትውልድ ኢትዮ መታወቂያ ካርድ/ቢጫ ካርድ/ የአገልግሎቱ ጊዜ አብቅቶ መታወቂያውን በወቅቱ ያላሳደሰ በየቀኑ የሚከፍለው መቀጫ ተጥሎበት ለተወሰኑ ወራት ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ ሆኖም የተወላጅነት መታወቂያቸውን በጊዜ ሳያሳድሱ የቆዩ የኢትዮጵያ ተወላጆች ያላሳደሱበትን ውዝፍ ክፍያ ሲጠየቁ አዲሱ መመሪያ ጊዜ ተሰጥቶት በሚገባ መልእክቱ ተላልፎ የማስተዋወቂያ ጊዜ ሳይኖር የውዝፍ ቅጣት መጠየቁ ትክክል እንዳልሆነ ቅሬታ እየቀረበ መሆኑ ይታወቃል፡፡ መንግስትም የተገልጋዩን ቅሬታ ግምት በማስገባት በመመሪያው ላይ የሚቀጥለው ማሻሻያ አድርጓል፡፡

በዚህም መሠረት **መታወቂያቸውን ሳያድሱ የእድሳት ጊዜ ያለፈባቸው የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ ከቅጣት ነፃ ሆነው የተወላጅነት መታወቂያቸውን እንዲያሳድሱ ተወስኗል፡፡**

በመሆኑ በተሰጠው የመሸጋገሪያ የጊዜ ገደብ ውስጥ የእድሳት ጊዜው ያለፈበትን የትውልድ መታወቂያ የያዛችሁ ሁሉ ከቅጣት ነፃ እንድታሳድሱ እናሳስባለን፡፡

**ከኢትዮጵያ ቆንስሌት**
**ሎስ አንጀለስ**